የኢትዮጵያ
ቡናና ሻይ ባለሥልጣን
ETHIOPIAN
COFFEE AND TEA AUTHORITY

ቁጥር፡-ኢት/ቡ/ሻ/ባ/ ሰ-036/216
Reference

ቀን፡- 06 ሐምሌ 2013 2013 ዓ/ም
Date

ለምርት ገበያ
ለኦሮሚያ ገበያ ልማት ኤጀንሲ
ለኦሮሚያ ክልል ግብርና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ
አዲስ አበባ
ለደቡብ ክልል ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን
ለሲዳማ ክልል ቡና ሻይና ቅመማ ቅመም ባለሥልጣን
ለደቡብ ክልል ግብርናና ተፈጥሮ ሀብት ቢሮ
በሲዳማ ክልል ግብርናና ተፈጥሪ ሀብት ቢሮ
ሀዋሳ
ለአማራ ክልል ግብርና ቢሮ
ባህር ዳር
ለቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል ግብርና ቢሮ
ቤንሻንጉል
ለጋምቤላ ክልል ግብርና ቢሮ
ጋምቤላ
ለቡና ላኪዎች ማህበር
ለደቡብ ቡና አቅራቢዎች ማህበር
ለኦሮሚያ ቡና አቅራቢዎች ማህበር
ለቡና ቆይዎች ማህበር
ለቡና አልሚ ላኪ ማህበር
ውመን ኢን ኮፊ ማህበር
ባሉበት

ጉዳዩ፡- **መመሪያ ስለመላክ**

በርዕሱ እንደተጠቀሰው የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን በደንብ ቁጥር 364/2008 ተቋቋሞ በአዋጅ ቁጥር 1051/2009 አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት መመሪያ የማውጣት ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡

በዚሁ መሠረት የቀጥታ ትስስር አቅርቦት የሽያጭ ውል አስተዳደር እና የዋጋ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 05/2013 ከሐምሌ 01/2013 ዓ/ም ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን የጸደቀ በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት በሙሉ ተግባራዊ እንዲያደርጉ እናስታውቃለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አዱኛ ደበላ ቡቴ (ፒኤች ዲ)
ዋና ዳይሬክተር

ግልባጭ
- ለግብርና ሚኒስቴር
- ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
- ለዋና ዳይሬክተር
- ለገበያ ልማትና ቁጥጥር ዘርፍ
- ለልማት ዘርፍ
- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ኢት/ቡ/ሻ/ባለሥልጣን

+251-115-31-40-06 +251-118-33-39-15 +251-115-31-40-97 5131
info@ethiocta.gov.et www.ethiocta.gov.et
BUNNA ENA SHAI BLDG
Addis Ababa, Ethiopia

እባክዎን መልስ ሲሰጡ የደብዳቤያችንን ቁጥር ይጥቀሱ
Please Quote our Reference When Replying

የኢትዮጵያ
ቡናና ሻይ ባለስልጣን
ETHIOPIAN
COFFEE AND TEA AUTHORITY

# የቀጥታ ትስስር የአቅርቦት ቡና ሽያጭ ውል አስተዳደርና የዋጋ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 05/2013

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Coffee & Tea Development & Marketing Authority

ሰኔ/2013

አዲስ አበባ

# የቀጥታ ትስስር የአቅርቦት ቡና ሽያጭ ውል አስተዳደርና

## የዋጋ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 05/2013

የቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 እና የሚኒስትሮች ምክር ቤት በቡና ግብይት እና ጥራት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 433/2011 ላይ የተደነገጉትን ድንጋጌዎችን ማስፈጸም በማስፈለጉ፤ ከላይ በተጠቀሰው አዋጅ አንቀጽ 24 ንዑስ አንቀጽ 2 ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህን የቀጥታ ትስስር የአቅርቦት ቡና ሽያጭ ውል አስተዳደርና የዋጋ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 05/2013 አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1.1 **አጭርርዕስ**

ይህ መመሪያ የቀጥታ ትስስር የአቅርቦት ቡና ሽያጭ ውል አስተዳደርና የዋጋ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 05/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

1.2 **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጓሜ የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **"አዋጅ"** ማለት የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1051/2009 ማለት ነው፡፡
2) **"ደንብ "**ማለት የቡና ግብይትና ጥራት ቁጥጥር ደንብ ቁጥር 433/2011 ማለት ነው፡፡
3) **"ውል"** ማለት፡- በወጪ ቡና አቅርቦት ግብይት ሂደት ውስጥ ሁለት እና ከዚያ በላይ በሆኑ ተዋዋይ ወገኖች የሚፈጸም ሕጋዊ የወጪ ቡና አቅርቦት ሽጭ የስምምነት ሰነድ ነው፡፡
4) **"የውል ስምምነት ይዘት"** ማለት፡- ተዋዋይ ወገኖች በውል ስምምነት ሰነዳቸው በአስገዳጅነት ሊያሟላቸው የሚገቡ የውል ቃሎች ናቸው፡፡
5) **"የወጪ ቡና አቅርቦት"** ማለት በኢትዮጵያ ምርት ገበያ እና በሌሎች ግብይት አማራጮች ለወጪ ገበያ የቀረበ ያልተዘጋጀ ቡና ማለት ነው፣
6) **"አቅርቦት ቡና"** ማለት በአምራች አካባቢ ባሉ ኢንዱስትሪዎች ተዘጋጅቶ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም ለኤክስፖርት ማዘጋጃ ኢንዱስትሪዎች በቀጥታ የሚቀርብ ቡና ነው፤
7) **"የወጪ ገበያ ቡና"** ማለት የአገሪቱን የወጪ ገበያ ቡና የጥራት ደረጃ መስፈርትና የገዢውን ፍላጎት በጠበቀ መልኩ በጥሬው፣ ተቆልቶ፣ ተፈጭቶ ወይም በሌላ መልኩ እሴት ተጨምሮበት የተዘጋጀ ቡና ነው፤

8) **"የትስስር ቡና አቅርቦት ሽያጭ ውል ምዝገባ"** ማለት ግብይት ፈፃሚ ወገኖች የተስማሙበት የቡና ሽያጭ ውል በሰነዶች ማረጋጋጫ አጀንሲ ወይም ሰነዶች ለማረጋገጥ ህጋዊ ሰውነት ወይም ውክልና የተሰጠው አካል የሚደረግ ምዝገባ ማለት ነው፣

9) **"ወቅታዊ የወጪ ቡና አቅርቦት ከፍተኛ ዋጋ"** ማለት በቡና ዓይነት፣የጥራት ደረጃ፣ ሽያጭ ዋጋ እና ወጪ በባለስልጣኑ ተወስኖ የሚሰላ እለታዊ ከፍተኛ ዋጋ ማለት ነው፣

10) **"ወቅታዊ የወጪ ቡና አቅርቦት ዝቅተኛ ዋጋ"** ማለት በቡና ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ የሽያጭ ከፍተኛ ዋጋ ላይ በመቶኛ ቅናሽ በባለስልጣኑ ተወስኖ የሚሰላ እለታዊ ዝቅተኛ ዋጋ ማለት ነው፣

11) **"የቡና አማራጭ ግብይት"** ማለት የቡና ግብይት ተዋንያንን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑ በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ የሚፈቀድ ከምርት ገበያው ውጪ የሚካሄድ የቡና ግብይት ነው፤

12) **"ቀጥታ ትስስር"** ማለት በባለስልጣኑ በህግ አግባብ በቀጥታ የግብይት ትስስር ለላኪ ወይም ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ግብይት ነው፤

13) **"ቡና አቅራቢ"** ማለት አግባብ ካለው የክልል አካል የብቃት ማረጋገጫና የቡና ንግድ ፈቃድ የተሰጠው ቀይ እሸት ወይም ጀንፈል ቡና በተፈቀደ የመገበያያ ስፍራ ወይም ህጋዊ የልማትና ግብይት ትስስር ከፈጠሩ አርሶ አደሮች በመግዛት ወይም ከራሱ ማሳ ወይም ህብረት ሥራ ማህበር ከሆነ ከአባላት በመሰብሰብና በማዘጋጀት ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ ወይም በህግ አግባብ በቀጥታ የግብይት ትስስር ለላኪ ወይም ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

14) **"የቡና ዓይነት"** ማለት በቡና ጥራት ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል ቡናው ካለው ጣዕምና መገኛ ባህሪ አንፃር ለመለያነት የተሰጠው ስያሜ ማለት ነው።

15) **"የጥራት ደረጃ"** ማለት የቡናው አመራረት፣ አዘገጃጀትና ጣዕም ተከትሎ አግባብ ባለው አካል የተሰጠው የጥራት ደረጃ ነው።

16) **"የቡና ምርት ዘመን"** ማለት የቡና ምርት ከተሰበሰበበት ጊዜ ጀምሮ የአንድ ዓመት ጊዜ ማለት ነው፣

17) "የወጪ ቡና አቅርቦት ዋጋ ማናበቢያ" ማለት አለም አቀፍ እና አገር አቀፍ የቡና ዋጋ ዝንባሌ አዎንታዊና አሉታዊ ሁኔታ ጋር ለማጣጣም በባለስልጣኑ የሚደረግ የቡና ዋጋ ማናበቢያ ማለት ነው፣

18) "የቡና መያዣ ጆንያ" ማለት እሽት ወይም ጆንፈል ወይም የአቅርቦት ወይም የኤክስፖርት ቡና ከቦታ ቦታ ለማዘዋወር ወይም ለማከማቸት ጥቅም ላይ የሚውል ከቃጫ ወይም ለቡና ተስማሚነታቸው አግባብ ባለው አካል በተረጋገጡ ግብዓቶች የተሰራ ከረጢት ነው፡፡

19) "የሦስተኛ ወገን ዳኝነት" ማለት በአቅራቢ.ና ላኪ. መካከል በተደረገ የቡና ሽያጭ ውል መሰረት ግብይት ፈፅመው በቡናው ጥራት ደረጃ ሳይስማሙ ቀርተው በቡና ጥራት፣ ምርመራና ሰርተፊኬሽን ማዕከል የሚሰጥ ጥራት ደረጃ የግልግል ዳኝነት ማለት ነው

20) አስተዳደራዊ እርምጃ" ማለት በዚህን መመሪያ የተደነገጉትን ተላልፎ ሲገኝ ባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል የሚወስደው እርምጃ ነው፡፡

21) "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

1.3. በአዋጅ 1051/2009 አንቀጽ (፪) እና በደንብ ቁጥር 433/2011 አንቀጽ (፪) የተመለከቱት ትርጓሜዎች ለዚህ መመሪያ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

1.4. **የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ማንኛውም የወጪ. ቡና ላኪ.ና የውጪ. የአቅርቦት ቡና አቅራቢ. ነጋዴ ላይ ተፈጻሚ. ይሆናል፡፡

## ክፍልሁለት
## የቀጥታ ትስስር የቡና ግብይት ውል አሠራር

**2/ የሽያጭ ውል ይዘት**

1) በትስስር የሚቀርብ የወጪ. ቡና የአቅራቢ.ነት እና የላኪ.ነት ፈቃድ አግባብ ካለው አካል በተሰጣቸው መካከል የሚደረግ ሽያጭ ውል በፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫ ኤጀንሲ. ወይም አግባብ ባለው በክልል አካል ይፀድቃል፡፡

2 )ቡና ሽያጭ ውል ሲ.ፈጸም የውሉ ሰነድ:-

ሀ/ የቡና አቅራቢ. እና ላኪ. ሙሉ ስም እና የሚገኝበት ሙሉ አድራሻ፣

ለ/ የቡናውን ዓይነት፣መጠን፣ሁሉም የወጪ. ቡና የጥራት ደረጃዎች፣

ሐ/ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በሚያወጣው የከፍተኛና ዝቅተኛ አማካይ ዋጋ ስሌት መሰረት ለሁሉም ቡና ጥራት ደረጃ እስከ 5% ጭማሪ፣

መ/ ውሉ የሚፈጸምበት ጊዜ፣

ሠ/ የገንዘብ አከፋፈል፣

ረ /የርክክብና የጥራት ምርመራ የሚደረግበት ቦታ፣

ሰ/ ቡና የሚጓጓዝበት ወጪ እና ሁኔታ፣

ሸ/ ውሉ በውልና ማስረጃ ኤጀንሲ ወይም አግባብ ባለው አካል ፀድቆ ለኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን በማቅረብ መመዝገብ አለበት፣

ቀ/ በተዋዋይ ወገኖች አለመግባባት ቢፈጠር የሚፈታበት የህግ አግባብ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለስልጣኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፤

3/ **የሽያጭ ውል አፈፃፀም**

1) የሽያጭውልለማስመዝገብ፣

ሀ/ ላኪው ከኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን የተሰጠ የታደሰ የላኪነት ብቃት ማረጋገጫ እና የታደሰ የላኪነት ንግድ ፈቃድ፣

ለ/ አቅራቢው ስልጣን ከተሰጠው የክልል አካል የታደሰ የአቅራቢነት ብቃት ማረጋገጫ እና የታደሰ የአቅራቢነት ንግድ ፈቃድ፣

ሐ/ በአንቀፅ 2 ከሀ-ሸ በተዘረዘረው መሰረት የተሟላ የቀጥታ ትስስር ቡና ግብይት የፀደቀ ውል ይዞ መቅረብ አለበት።

መ/ ተዋዋዮች በሚፈልጉት ቡና ዓይነት፣ደረጃ እና መጠን ጠቅሰው መዋዋል ይችላሉ፣

ሠ/ ባለስልጣኑም የቀጥታ ትስስር ግብይት ስምምነት መዝግቦ ለተዋዋዮች እና ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል።

4/ **የቀጥታ ትስስር ቡና ሽያጭ ውል የመፈጸሚያ ጊዜና ሂደት**

1) የሽያጭ ውል መፈጸሚያ ጊዜ በደንቡ ላይ በተደነገገው መሰረት ተፈፃሚ ሆኖ የምርት ርክክቡ በምርት ዘመኑ ብቻ ይፈፀማል፣

2) ማንኛውም የትስስር ቡና ሽያጭ ውሉ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ፣ጥራት፣መጠንና ዋጋ መሠረት መፈጸም ይኖርበታል፣

3) በሽያጭ ውል መሰረት አለመፈጸሙ ከተዋዋዮች አንዱ ለባለስልጣኑ ከበቂ መረጃ ጋር ባቀረቡ ጊዜ፤

ሀ/ ያልፈፀመው ላኪ ከሆነ ከሌሎች የወጪ ቡና አቅራቦት ግዢ ውል እንዳይፈጽም እና የወጪ ቡና ሽያጭ ውል እንዳይፈፅም ለብሄራዊ ባንክ፣ ለምርት ገበያ፣ለክልል፣ ለአቅራቢና ላኪ አደረጃጀቶች ባለስልጣኑ እንዲያውቁት በማድረግ አስተዳዳራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

ለ/ ያልፈፀመው አቅራቢ ከሆነ የወጪ ቡና አቅርቦት ሽያጭ ውል እንዳይፈጽም ለሚመለከታቸው ለክልል፣ ለኢትዮጵያ ምርት ገበያ፣ ለአቅራቢና ላኪ አደረጃጀቶች ባለስልጣኑ እንዲያውቁት በማድረግ አስተዳዳራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

ሐ/ በአንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ውሉ ለመፈጸም የማያስችል ስለመሆኑ፣ አስገዳጅ ወይም ያልተጠበቀ ምክንያት ከተዋዋዮች አንዱ ወይም ሁለቱም ለባለስልጣኑ ሲያመለክቱ ውላቸውን ሰርዘው ሲቀርቡ ምዝገባው ይሰርዛል፣

## ክፍልሶስት
## የቀጥታ ትስስር የቡና ግብይት የገንዘብ አከፋፈል

5/ **የቀጥታ ትስስር ቡና ግብይት ክፍያ አፈፃጸም፣**

ሀ/ ቡናው በባለስልጣኑ ሽኝት ጣቢያ ቀርቦ በላኪው ወይም በህጋዊ ወኪሉ ርክክብ በተደረገ በሦስት የሥራ ቀናት ውስጥ ሙሉ ክፍያውን ለአቅራቢው ይፈፅማል፣ ካልተፈፀመ ቅሬታውን በአምስት የሥራ ቀናት አቅራቢው ለባለስልጣኑ ያሳውቃል

ለ/ ቡናው በባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ሽኝት ጣቢያ ቀርቦ የጥራት ደረጃ ተሰጥቶ የሚሸኝ ከሆ ነላኪው በራሱ ወይም በህጋዊ ወኪሉ ቡናውን እንደተረከበ በዕለቱ ክፍያ ይፈፅማል፣ ካልተፈፀመ ቅሬታውን በሦስት የሥራ ቀናት ለባለስልጣኑ ያሳውቃል፣

ሐ/ ላኪው ክፍያውን በተቀመጠው ጊዜ ሳይፈፅም ቀርቶ ዋጋ የጨመረ ከሆነ በወቅቱ እለታዊ ዋጋ ተሰልቶ የሚከፍል ሆኖ ዋጋው ከቀነሰ በውሉ መሰረትተፈፃሚ ይሆናል፣

መ/ አቅራቢው ቡናውን በተቀመጠው ጊዜ ሳያቀርብ ቀርቶ ዋጋ የጨመረ ከሆነ በውሉ በተጠቀሰው ዋጋ የሚያስረክብ ሆኖ፣ ዋጋው ከቀነሰ በእለታዊ ዋጋ ተሰልቶ ቡናውን ያስረክባል፣

ሠ/ አቅራቢው በውሉ መሰረት በቡና ዓይነት፣ የጥራት ደረጃ፣ መጠን እና ጊዜ ውስጥ ለላኪው የማያቀርብ ከሆነ ላኪው በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ለባለስልጣኑ ቅሬታውን ያቀርባል፣

ረ/ ከላይ በአንቀፅ 5 በንዑ ስአንቀፅ ሀ እና ለ እደተጠበቀ ሆኖ አስገዳጅ ሁኔታ ስለማጋጠሙ ከሚመለከተው አካል ማስረጃ ካቀረበ ክፍያው እስከ አንድ ሣምንት መራዘም ይችላል።

ሰ/ ማንኛውም የመንግስት ገቢ በገቢዎች አዋጅና ደንብ መሰረት የሚፈፀም ሆኖ ዊዝሆልዲንግ ታክስ ላኪው ከአቅራቢው በመሰብሰብ ለሻጩ ደረሰኝ ይሰጣል ለመንግስት ገንዘቡን ገቢ ያደርጋል፣

ሸ/ ላኪው ክፍያን በባንክ በኩል በመፈፀም የክፍያ ሰነድ ቅጂ በማያያዝ ለአቅራቢው ይሰጣል፣ አቅራቢው የሽያጭ ደረሰኝ በሁለት የሥራ ቀናት ውስጥ ለላኪው ያስረክባል፣

ቀ/ ከላይ በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ ሰ እና ሸ የተጠቀሰውን ተፈፃሚ ያላደረገ አካል በአገሪቷ ገቢ ህግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል፣

## ክፍል አራት
## በቀጥታ ትስስር ቡና የሚጓጓዝበት እና የርክክብ አሰራር

6/ **የቀጥታ ትስስር ቡና ሽኝት አሰራር**

1) የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ማዕከል፣

ሀ/ የቀጥታ ትስስር ቡና ተዘጋጅቶ ወደ ኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ቅርንጫፍ ሽኝት ጣቢያ እንዲሸኝለት በፅሁፍ ወይም በቃል ለወረዳው የጥራት ቁጥጥር ሙያተኛ ያመለክታል፣

ለ/ ለማጓጓዝ ያዘጋጀው መኪና ቡና ለማጓጓዝ ብቁ መሆኑን የጥራት ቁጥጥር ሙያተኛ ያረጋግጣል፣

ሐ/ እያንዳንዱ ኬሻ ቡና ከመጫኑ በፊት ተመዝኖ እንዲጫን በማድረግ ጠቅላላ የተጫነው ቡና መጠንና ደረጃ መረጃ በመያዝ በሽኝት ሰነድ ላይ ይመዘግባል፣

መ/ በአቅራቢያው ወደሚገኝ ለባለስልጣኑ ቅርንጫፍ ሽኝት ጣቢያ በሽኝት ሰነድ ተገልጾ እና ታሽጎ ይሸኛል፣

2) የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን ቅርንጫፍ ሽኝት ጣቢያ

ሀ/ የመጀመሪያ ደረጃ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ማዕከል፣ የተሸኘው ቡና ከተሸኘበት ሰነድ ጋር በማመሳከር በትክክል ታሽጎ መድረስ በሚገባው ጊዜ መድረሱን የቅርንጫፍ ሽኝት ጣቢያው ሙያተኛ ያረጋግጣል፣

ለ/ የታሸገበት ፕሎንፕ በሚቀይሩበት ጊዜ ተጨማሪ ባዕድ ነገሮች አለመጫኑን ማረጋገጥ፣

ሐ/ በአካባቢው የምድር ሚዛን ካለ ክብደቱን በመለካት ወይም በወረዳው ክብደት መጠን በመውሰድ የሽንት ጣቢያው ወደ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ በላኪው ስም በድጋሚ በፕሎምፕ በማሸግ ይሸኛል፤

7/ የቀጥታ ትስስር ቡና ግብይት የጥራት ደረጃና የርክክብ አሰራር

1) ላኪው በውሉ መሰረት የቡናውን ዓይነት፣መጠን፣የጥራት ደረጃ መሟላቱን አረጋግጦ በሸኝት ጣቢያ ይረከባል፣

2) ጥራት ደረጃ የሚሰጠው ሁለቱ ተዋዋይ ወገኖች በራሳቸው ስምምነት የሚከናወን ሲሆን ካልተስማሙ በባለስልጣኑ በሚሰጠው የጥራት ደረጃ መሰረት ይሆናል፣

3) ላኪው ምርቱ ከተረከበ በኃላ እያንዳንዱ ጆንያ ዋጋ ተሰልቶ ከቡና ክፍያ ጋር አብሮ ለአቅራቢ ይከፈላል፣

4) ከቡና መነሻ ወረዳ እስከ ባለስልጣኑ ሸኝት ጣቢያ ድረስ የትራንስፖርት ወጪ በአቅራቢው ይከፈላል፣ ከባለስልጣኑ ሸኝት ጣቢያ እስከ ወጪ ቡና ማዘጋጃና ማከማቻ ላኪው ይከፍላል ለፍጥነቱ፣ ወጪ ለመቀነስ እና ለቡናው ጥራት ሲባል በሁለቱ አካላት ስምምነት ከመነሻው ተጭኖ በመጣበት መኪና ይሸኛል ወይም በጋራ ስምምነት ይፈፀማል፣

## ክፍል አምስት
## የወጪ የአቅርቦት ቡና ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ዋጋ አወሳሰን

8/ወቅታዊ የወጪ የአቅርቦት ቡና ዋጋ አወሳሰን

1) የከፍተኛ ቡና ዋጋ አወሳሰን

ሀ/ በመጀመሪያ ቡና ግብይት ማዘጋጃ ኢንደስትሪ የተዘጋጀ የታጠበ፣ ያልታጠበ ወይም የልዩ ጣዕም ቡና ምርት የግዢ፣ የዝግጅት፣ የማጓጓዢያ፣ የትርፍና ሌሎች ተያያዥ ወጪዎችታሳቢ ያደረገዋጋ፣

ለ/ በአለም አቀፍ የተመሳሳይ ቡና ዓይነትና ደረጃ እንዲሁም የኢትዮጵያ ላኪዎች ለአለም ገበያ የሸጡበት መጠንና ዋጋ ጥቅል መካከለኛ ወይም ዌይትደአቨሬጅ በማስላት፣

ሐ/የአለም አቀፍ የገበያ አቅርቦት፣ የአገር ውስጥ አቅርቦት፣ ክምችት፣ ቀሪ የቡና ግብይት ጊዜን እና ሌሎች አገር አቀፍና አለም አቀፍ አዎንታዊና አሉታዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ያስገባ እለታዊ፣ ሳምንታዊ እንዲሁም በአስፈላጊነት የጊዜ ገደብ የአቅርቦት ቡና ዋጋ በባለስልጣኑ ይወሰናል።

2) ዝቅተኛ ቡና ዋጋ አወሳሰን በአንቀፅ 5 ንዑስ አንቀፅ 1 ሀ፣ ለ እና ሐ በተጠቀሱት አግባብ የከፍተኛ የአቅርቦት ቡና ዋጋ አወሳሰን መሰረት የተወሰነውን በአስፈላጊነት በመቶኛ በመቀነስ ዝቅተኛ ዋጋ ይወሰናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የቡና አምራች ክልሎች ተግባርና ኃላፊነት

9/ በየደረጃው የሚገኙ የክልል አካላት በዚህ መመሪያ በተቀመጠው መሰረት ለአቅራቢ የተቀመጠውን ግዴታ የመከታተል፣ የማስፈፀም፣ የመቆጣጠር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፣

ሀ/ በቀጥታ ግብይት ትስስር የሚሳተፉ አቅራቢዎች ከመተሳሰራቸው በፊት ክልሉ ወይም አግባብ ያለው የክልል አካል በምርት ዘመኑ በአቅራቢነት ለመስራት የብቃት ማረጋገጫ ያሳደሱ መሆኑን ያረጋግጣል፣

ለ/ የመጀመሪያ ደረጃ የግብይት ማዕከላትና ማጠቢያና መቀሸሪያ እንደስትሪዎች በምርት ዘመኑ ቡናን ለማዘጋጀት ብቁ ስለመሆናቸው ያረጋግጣል፣

ሐ/ በማዕከላቱ የሚደረጉ የግብይትና የሽኝት አሰራሮችን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

መ/ በደንብ ቁጥር 433/2011 መሰረት የቡናን ቆጠራን በማካሄድ የምርት ክምችት ሚዛኑን ለባለስልጣኑ ያሳውቃል፣

ሠ/ ቡናው ከወረዳ ስጫን ተመዝኖ፣ መሰረታዊ የጥራት ደረጃው ተለይቶና ተመዝግቦ በትስስር አቅራቢው ውል ለገባለት ላኪ ወደ ሽኝት ጣቢያ ስለመላኩ ያረጋግጣል፣

መ/ ውሉን በጥራት ደረጃ፣ በመጠን፣ በቡና ዓይነት እና በጊዜ ገደቡ ያልፈፀመውን አቅራቢ በመመሪያው በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ ከለ-መ ላይ በተቀመጠውና በክልል አካሉ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፣

## ክፍል ሰባት

## አስተዳደራዊ እርምጃዎች

10/ ተዋዋይ ወገኖች የዚህን መመሪያ ለማስፈጸም የወጡ ድንጋጌዎችን ተላልፍ ሲገኙ በባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ባለው የክልል አካል ጉድለቱን ለማስተካከል፡

ሀ/ ያልፈጸመው ላኪ ከሆነ ባለስልጣኑ በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ክፍያውን እንዲፈፅም የማስጠንቀቂያ ደብዳቤ እንዲደርሰው ለላኪው ይሰጣል፣

ለ/ ያልፈጸመው አቅራቢ ከሆነ ለባለስልጣኑ ቅሬታ በቀረበ በሁለት ቀን ውስጥ አግባብ ላለው ለክልል አካል በማሳወቅ ክልልም በአምስት የሥራ ቀናት ውስጥ ቡና እንዲያስረክብ የማስጠንቀቂያ ደብዳቤል አቅራቢው ይሰጣል፣

ሐ/ ሁለቱም ተዋዋዮች በአንቀፅ 9 ንዑስ አንቀፅ ሀ እና ለ መሰረት ካልፈፀሙ ባለስልጣኑ የላኪን የብቃት ማረጋገጫ ያግዳል፤ በተመሳሳይ አግባብ ያለው የክልል አካል የአቅራቢን የብቃት ማረጋገጫ ያግዳል፣

መ/ በተዋዋይ ወገኖች በዉሉ መሠረት አለመፈፀሙ ለባለሥልጣኑ ወይም አግባብ ላለዉ ለክልል አካል ቅሬታ ባይቀርብም በሚደረገዉ የዉል አፈፃጸም ክትትል ባለሥልጣኑም ሆነ አግባብ ያለዉ ክልል አካል ካረጋገጠ የላኪን ወይም የአቅራቢን ብቃትማረጋገጫ ሊያግድ ይችላል

## ክፍል ስምንት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

11/ የመተባበር ግዴታ

በዚህ መመሪያ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ የተገለፀ ሰው በማስፈፀምና በመፈጸም ረገድ ከባለስልጣኑ ወይም አግባብ ካለው የክልል አካል ጋር የመተባበር ግዴታ አለበት፡

12/ የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች፡

ይህ መመሪያ ከመፅደቁ በፊት የተፈፀሙ የወጪ ቡና ሽያጭ ውሎች ላይ ተፈፃሚ አይሆኑም፡፡

13/ የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ይህንን መመሪያ ማሻሻል ይችላል፡፡

14/ መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ፡

ይህ የወጪ ቡና ሽያጭ ውል መመሪያ ከሀምሌ 1/2013 ዓ.ም.ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

አዱኛደበላ (ፒ.ኤች.ዲ)

ኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር

ሰኔ 30/2013 ዓ.ም.

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Coffee & Tea Development & Marketing Authority

# የቀጥታ ግብይት ትስስር (VERTICAL INTEGERATION/ ውል ስምምነት

1. የተዋዋይ ወገኖች መረጃ

| መግለጫ | | ገዥ/ላኪ/ | ሻጭ/አቅራቢ/ |
|---|---|---|---|
| ሥምና አደራሻ | የድርጅቱ ሥም | | |
| | የንግድ ሥራ ፈቃድ ቁጥር | | |
| | የንግድ ምዝገባ ቁጥር | | |
| | ክልል | | |
| | ዞን/ክ/ከተማ | | |
| | ወረዳ | | |
| | ቀበሌ/ቤት ቁጥር | | |
| | ስልክ ቁጥር | | |

2. የውሉ ዝርዝር መግለጫ

| ተ.ቁ | የቡናው ዓይነት | የጥራት ደረጃ | መጠን በቶን | ከእለቱ ዋጋ ተጨማሪ የሚጨመረው ዋጋ በ (%) | የውሉ ጊዜ | | የመረከቢያ ጣቢያ ሥም | ደረጃ የሚሰጥበት ቦታና የሚሰጠው አካል |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | ውል የተገባበት ቀን | ውሉ የሚጠናቀቅበት ቀን | | |
| | | | | | | | | |

3. የውሉ ተፈጻሚነት

- በውል ሰጭ እና ውል ተቀባይ ወይም በቡና ገዥና ሻጭ መካከል ስለሚኖሩ መብትና ግዴታዎች የቀጥታ ትስስር የአቅርቦት ቡና ሽያጭ ውል አስተዳደርናየዋጋ አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 05/2013 ላይ በተዘረዘረው መሰረት ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
- በውል አፈፃፀም ሂደት ውል ሰጪ እና ውል ተቀባይ አለመግባባት ቢከሰት በድርድር ወይም አግባብ ባለው ፍ/ቤት ለመዳኘት ግራ ቀኛችን ተስማምተናል፡፡

4. ህጋዊ ድንጋጌዎች

- ይህ ውል በፍታብሔር ህግ ቁጥር 1731 እና 2005 መሰረት በህግ ፊት በውል ሰጪና ውል ተቀባይ መካከል በአዲስ አበባ ከተማ ------ ክፍለ ከተማ ወረዳ --- ስምምነት የተፈጸመ ሲሆን ከዛሬ ------ ቀን ----- ወር ----- ዓ.ም. ጀምሮ ውሉ እስከሚጠናቀቅ ድረስ የጸና ይሆናል፡፡

ይህ ውል ውል ሰጪ

-----------------------------

ውል ተቀባይ

------------------------

The Federal Democratic Republic of Ethiopia Ethiopian Coffee & Tea Development & Marketing Authority